# ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ ውጤቱን ባለመቀበል ህዝቡን ለትግል ለማነሳሳት አቋም ወሰዱ

ቅንጅትና ህብረት ሰሞኑን በሰጡት መግለጫ ምርጫው ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ ማጣራት ያለው ሂደት ዴሞክራሲያዊ ባለመሆኑ ውጤቱን እንደማይቀበሉና ጥያቄያቸውን ተቀብሎ ህዝቡ ለትግል እንዲነሳሳ እንደሚንቀሳቀሱ ተናግረዋል።

«ከዚህም ሌላ አሁን ከገባንበት አጣብቂኝ መውጣት እስከምንችል ድረስ እርዳታችሁ እንዳይለን» ሲሉ ፓርቲዎቹ የብሄራዊ አንድነት መንግስት የመመስረት ጥያቄን ባቀረቡበት ሰነድ ላይ ህዝቡን ጠይቀዋል።

በዚህም ሰነዳቸው ላይ «በፖለቲካ ድርጅቶች መሀከል ያለው አለመግባባት ቅጥ ወደ አጣ አመፅና ግጭት ከተቀየረ ማረጋጋቱ ለሁላችንም እጅግ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው» ሲሉ አትተዋል።

የቅንጅቱ ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ሃይሉ ሻውል እስከ አሁን ድረስ በምርጫ መወዳደራቸውና በማጣራቱ ሂደት መሳተፋቸው እንደፀፀታቸው ገልፀው ከአሁን በኋላ በድጋሚ ምርጫው እንደማይሳተፉና መፍትሄ ለማግኘት ወደ ፍርድ ቤት እንደማ ይሄዱ ተናግረዋል። በሌላ በኩል ቅንጅት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዳ ሸነፈና ኢህአዴግ እንደተሸነፈ ተናግረዋል። ጰ